ለሸንፈቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደነበራቸው ይገልፃሉ:: ከዚህም በተጨማሪ ፤ ከየአገሪቱ ጆኦግራፊ ጀምሮ እስከ የሰራዊቱና የፖርቲው ዝምድና የእዝ አወቃቀሩ፤ የጦሩ ጠቅላይ አዛዥና ሌሎች የፖለቲካ ስልጣን የነበራቸው መሪዎች ጣልቃ ገብነት ወዘተ ይዘረዘራሉ:: እነዚህ ለሸንፈቱ አስተዋጽኦ እንደነበራቸው የሚካድ አይደለም:: ጉዳዩ ግን ፖሊሲዎቹ ከምን መነጩ ነው? የስርዓቱ ፀረ ዲሞክራሲያዊነት የፈጠራቸው ናቸው:: ደርግ አንደ ፖከለቲካዊ ኃይል ማድረግ ይችል የነበርው፤ ያደረገውን ነው::

ህወሓት የአማልክት ስብሰብ አልነበርም የሰዎች ስብሰባ ነው:: ከምን ዓይነት ሐ/ስብ እነደወጣም ይታወቃል:: ሆኖም በሚመራው ህዝብና በታጋዮች ዘንድ ለፍትህ ለእኩልነት ለዲሞክራሴያዊ ስርኣት ግንባታ ነው የምንታገለው የሚል ፅኑ እምነት ነበረው:: እንደዛ በመሰለው አስቸጋሪ ሁኔታ ምልአት ህዝቡን እንዲከት ያደረገውና ከፍተኛ ብቃት ያለው ሰራዊት እንዲገነባና በጀግንንት እንድዋጋ ያደረገው መሰረትዊ ምክንያት ይህ ነው::

ህወሓት ምንም አንከን አልነበረውም፤ ከዲሞክራሲያዊ መሆን አንፃርም ጎድሎ የለሽ ነበር ባልልም፣ ከደርግ መንግስት ጋር በእኩል ማስቀመጥ ግን አይቻልም:: ህወሀት ከደርግ መንግሰት ጋር ሲንጻጸር መሠረታዊ ልዩነት አልነበረውም ከተባለ ፀሐፊው ወደ ማጠቃለያ አካባቢ (329-333) አሁን ያለውን ፖለቲካዊ ስርዓት ሲገልፁ ያስቀመጡትን ቀደም ብለው ከገለፁት ምዘና ጋር ማስታረቅ ይከብዳል::

ይህንን ሁኔታ ማለትም የአንድ ስርአት ፖለቲካዊ ባህርይና ከዛ ጋር እጅግ የተቆራኙት እንደየስራዊት ግንባታና ስምሪት፤ ጦርነት ማካሄድ፤ የመሰሉ ጉዳዮች ያላቸውን ተያያዥነትና ዝምድና በተገቢው መንገድ መገንዘብ በሃገራችን ሊኖር የመንፈልገውን የሰላም፣ የዲሞክራሲያዊ፤ የኦኮኖሚያዊና፤ ማኅበራዊ ብልፅግና ማለፍ ወይም አለማለፍ ጋር የተያያዙ ናቸው:: ስለዚህ እንደ ታሪክ ብቻ ሳይሆን እንደ የወደፊት አቅጣጫ ጠቋሚም ተፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው ብዬ አምናለሁ::

## 3. ወታደራዊ ፍልሚያዎች

የማተኩረው በስሜኑ የሀገራችን ክፍል ስለተደረጉት ወግያዎች ነው:: የማውቀው ይህንኑ ነው::

የመጀመሪያው ጥያቄ ፀሐፊው ውጊያወቹን ከምን አንፃር መረጥዋቸው የሚለው ነው:: ለዚህ መልስ ሰጥተዋል:: በደርግና በአማፅያኑ መሀከል በተደረገው ጦርነት ሁኔታውን በመሠረቱ ለመለወጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበራቸው ብለው

የሚያምኑባችን ጦርነቶች መርጠዋል። ብዙዎቸ ወግያዎች በሻቢአያና በደርግ የተደረጉ ናቸው። ትግራይ ውስጥ ሽሬ ላይ የተደረገው ጦርነትም ማን ወሳኝ ተራ ነበርው የሚለውን ጥያቄ ያነሱና መለሰን ለታሪክ ይታዉታል። (ገጽ 282) ሌሎቹን ኢህአዴግ ብቻውን በማህል አገር የፈፀምንቸውን ፍልሚያዎች አግረ መንገዳቸውን ይነካኩዋቸዋል። የመጨረሻውችን ተከታታይ ዘመቻወች ደግሞ የመቀረም፤ ዉጊያወችን ይልዋቸዋል።

ከዚህ በመነሳት የደርግ ሽንፈት ከማምጣት አንፃር ወሳኝ የነበረው ሁኔታ ስርዓቱ ፀረ ዲሞክራሲያዊ ስለነበር ይህ የፈጠራው ፖለቲካዊ ሽንፈት ነው ብዩ አምናለሁ። ሻህብያ በሳህል ተራራዎች ያደረጋቸው ውጊያዎች ለደርግ መንግስት ውድቀት አስተዋፅኦ አድርገዋል እንጂ ወሳኝ አልነበሩም። ጦርነቶቹ በተለይ ደግሞ በሽምቅ ዉጊያ የተካሄዱት የእርስ በርስ ውግያ እንዴት ነው የሚመዘኑት የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል። ይህ ማለት ባስመዘገቡት ወታደራዊ ድል ብቻ ነው ወይስ ወታደራዊ ፍልሚያዎቹ የሚመሩበት እስትራቴጂ የመንግስቱን ባህርይ በየግዜው እየጋለጠ ለመጨረሻ ሽንፈት እየበጃጀው ከመሄድ አንፃር ባላቸው አስተዋፅኦም ጭምር ይመዘናሉ ብሎ መጠየቅ ይገባል።

በጸሀፊዉ በሻቢያና በአህአዴግ ወታደራዊ ስትራቴጂ መጠነኛ ልዮነት ቢኖረውም ከልዩነቶቹ ይልቅ የሚያመሳስላቸው የበለጠ እንደነበረ ተገልጧል። እኔ ግን በሚከተሉት ወታደራዊ ቴክኒክ ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም የሚከተሉት ወታደራዊ ስትራቴጂ ግን መሠረታዊ ልዩነት ነበረው እላለሁ።

ሻህቢያ ከህዝብ ተነጥሎ የአንደኛው የዓለም ጦርነት በሚመስል የተያያዘ ምሽግ ውስጥ ሆኖ ቋሚ ጦርነት በማድረግ የደርግን መንግስት አዳክም ዓላማውን ለማሳካት ይመኝ ነበር።

ህወሓት/አህአዴግ ደግሞ ደርግን ከህዝብ እየነጠለ በማዳከም የሚደርግ የህዝባዊ ጦርነት ስተራቴጂን ይከተል ነበር። ይህንን በግልፅ ለማየት በተለይ ከ1980 ዓ.ም በኋላ የተደረጉትን የህወሃት/ኢህአዲግ ዘመቻወች መመርምርና በስርዓቱ ላይ የፈጠሩትና ተፅእኖ ማየት ጠቃሚ ይሆናል።

የዘመቻወቹ ባህርይ እንደኛው ዘመቻ ቀደም ብሎ የተካሄደውን ዘመቻ ተንተርሶ ለደርግ መንግስት ፋታ ሳይሠጥ፤ ከቁስሉ ሳያገግም በተከታታይነትና ግለታቸውን (momentum) ጠብቀው የሚፈጸሙ ነበሩ።

1980 (የካቲት-መጋቢት) ዘመቻ ድልደል ህወሓትን ወደ ወሳኙ የትግራይ ደጋማ ቦታወች በማዉጣት በትጥቅና ፖለቲካዊ መሰረት እንዲደላደል ያደረገ ዘመቻ ነበረ። የተጠናቀቀውም 17ኛ ክ/ጦርን ሙሉ በሙሉ የ16ኛ ክ/ጦር ሁለት

ብርጌዶችን /22ኛ-128ኛ/ የ 3ኛ ክ/ጦር ሁለት ብርጌዶችን በከፍተኛ ደረጃ ከጎሳቀለ በኋላ ነበር፡፡

በዚሁ 1980 በግንቦት ወር "የጣምራ ክንዳችንን" ዘመቻ 1ኛ ክ/ጦርን ሙሉ በሙሉና የሌሎች ክ/ጦርን ብርጌዶችን በከፍተኛ ደረጃ ያዳከመ ዘመቻ፤ ከአላጌ እስከ አላማጣ ያለውን ቦታ ለሁለት ሳምንታት በመዝጋት በደርግ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ የፈጠረ ዘመቻ ነበር፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ከ1980 ዓ.ም ክረምት ጀምሮ ደረጃ በደረጃ የ604 ኮርን ከሌሎች ኀይሎች ከኤርትራ፤ ከጎንደር፤ ከመቀሌ፤ ሙሉ በሙሉ በመነጠልና በማዳከም የተጠናቀቀዉ ዘመቻ ነበር፡፡

ከስድስት ወር በኋላ ደግሞ በ1981 ነሐሴ ተጀምሮ 1982 መስከረም መጀመሪያ ላይ የተጠናቀቀው ከደቡባዊ ትግራይ (ማይጨው እስከ ሰሜን ወሎ፤ወልዲያ) ድረስ ሰፍሮ የነበረውን የሦሥተኛ አቢዮታዊ ሰራዊት ቀዳሚ መምሪያንና የ 605 ኮርን ሦስት ለ/ጦሮች ከሁለት ሜካናይዝድ ብርጌዶች ጋርና በኋላ ለድጋፍ ከመጡጥ የ102 አየር ወለድ ብርጌዶች ጋር በመደረብ ከጥቅም ውጭ ያደረገው ለአስር ቀናት ያለማቋረጥ የተደረገው "የሰላም በትግል" ዘመቻ ተከናወነ፡፡ ይህ ዘመቻ ኢህአዴግ በከፍተኛ ደረጃ ወደ መሃል አገር እንዲገባ በር ከፈተ፡፡

ወደያው በመቀጠል በመስከረም 1982 ተጀምሮ እስከ የካቲት ወር የዘለቀው ዘመቻ "ፋና ኢህአዴግ" ተካሄደ፡፡ ይህ ዘመቻ የኢህአዴግ ሰራዊት የወልድያን ግንባር ወደ ምስራቅ በመተው ወደ ደቡብ ወሎና ሰሜን ሸዋ ምስራቅ ጎንደር እንዲዘልቅ ያስቻለና የደርግን መንግስት ደግሞ ከዚህ ሰፊ አካባቢ እንዲወገድ ያደረገ ዘመቻ ነበረ::

ዘመቻ ፋና ኢህአዴግ በወታደራዊ ስራውም አንፃር የደርግ ሰራዊት ግንባሩን ለማጠፍ ከደሴ ከተማ በሁለት አቅጣጫ (በሀይቅና ወረኢሉ) በኩል ከባህር ዳር ከተማ ደግሞ በጉና ተራራ በኩል ከሰሜን ሸዋም ከጣርማ በርና ከለሚ በኩል ያደረጋቸውን ሰፋፊ ሙከራዎች አዳክሞ በመጨረሻ የ603ኛ ኮር ከሶስት በላይ ክ/ጦሮችና የእነዚህ ክ/ጦሮች ተደራቢ ብርጌዶችን ከስራ ውጭ በማድረግ ሰፊ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ኪሳራ በደርግ መንግስት ላይ ያከናነበ ዘመቻ ነበር!!

በ1982 ክረምት ደግሞ ከኤርትራ ተጨማሪ ክ/ጦሮችን በማምጣት ኢህአዴግን ከደቡብ ወሎ እና ሰሜን ሸዋ ለመጥረግ ያደረገው ከ19 ብርጌዶች በላይ የተሳተፉበት